በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# ክፍል ስድስት


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ሰኔ ፳ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*አንድነት*

- ጌታችን ‹‹ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም፥ እነርሱም በዓለም ናቸው፥ እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው። … እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል።›› *ዮሐ 17፡11፣ 22-23።* እንዳለን በቤተ ክርስቲያን ግለኝነት (ለእኔ ብቻ) የሚል ሕይወት የለም።
- *በሐዋርያት ሥራ 4፡32* ‹‹*ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው፥ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም አልተናገረም*።›› እና ‹‹ በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር። ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ። *ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር*። በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።›› *የሐዋ 2፡42-46።* እንደተጠቀሰው ይህ አንድነት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያንም በግልጽ ይታይ ነበር።

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

- በዕለተ ጰንጠቆስጤም የነበረውን አንድነት ወይም ኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ አስማምቶ አቅርቦታል፡፡ ‹‹በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፡፡›› እንዲሁም ‹‹ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ትኵር ብሎ ወደ እርሱ ተመልክቶ፡፡ ወደ እኛ ተመልከት አለው፡፡›› *የሐዋ 3፡4፡፡*
- ቤተ ክርስቲያናችንም ስለ አንድነት ትጸልያለች፡፡ የአንዱ ራስ የኢየሱስ ክርስቶስ አካላት የሆኑ ምዕመናንን ሁሉ ከአንዱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም እንዲሳተፉ በማድረግ አንድነቱን (ኅብረቱን) ጠብቃለች ታስጠብቃለች፡፡
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፡፡ እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም በኵር ነው፡፡›› *ቆላ 1፡18*፣ ‹‹ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ፡፡›› *ኤፌ 5፡23፡፡*
- በዚህም አስደናቂ አንድነት መካከል ስለአካሉ ስለቤተ ክርስቲያን ራሱን የሰጠ መሥዋዕት የሆነ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን እናገኘዋለን፡፡
- ይህም የመሥዋዕትነት ሥራ ከዚህ አስቀድሞ ለአንድ ጊዜ ተደርጎ የቀረ ሳይሆን ዛሬም ቢሆን በየቅዳሴው የምንፈጽመው በሕይወታችንም የምናገኘው ነው፡፡
- በቅዳሴ የተወደደውን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን፣ ትንሣኤውን እየመሰከርን፣ እንገናኘዋለን፡፡

# <u>በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች</u>

***<u>ፍቅር</u>***

- ***ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመለከት በሰማይም በምድርም የሚገኙ ተከታዮችዋን በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አድርጋ በፍጹም ፍቅር የሰበሰበችበትን ውብ ሥዕሏን እንመለከታለን፡፡***
- ***ቅዳሴ የሚያስቀድሱ ሁሉ በቅዳሴው ካህኑ ስለ ሕያዋኑም ሆነ ስለሙታን፣ ስለባልቴቶችና ስለባለ ትዳሮች፣ ስለ መንገደኞችና ተገኝተውም በማስቀደስ ላይ ስለሚገኙት፣ ስለታመሙትና ስለጤነኞች፣ ስለድሆችና ስለ ባለጠጎች፣ ስለ ወንዝ ውሃና ስለ ነፋስ፣ ስለምድር ፍሬና ስለዝናም፣ የሚያስባቸውም ስለሌላቸው፣ ስለቤተ ክርስቲያንና ስለ መሪዎች … በሚያስደስትና ልብን በሚመስጥ ዜማ የሚጸልየውን የፍቅር ጸሎት ይሰማሉ፡፡***
- ***በርግጥም ቅዳሴ የፍቅር ምስጋና ነው፤ ቀዳስያኑም ሆኑ አስቀዳሾቹ በክርስቶስ አንድ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን አንድ ሆነው የሚተሳሰቡበት የሚጸልዩበትም ነው፡፡***
- ***በቤተ ክርስቲያን ያለው አንድነት በቤታችሁ በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወዴት አለ? ኦርቶዶክሳውያንን ሁሉ በአንድ ፍቅር ያስተሳሰራቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውስ ፍቅር በቤታችሁ በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቤተሰቡን ሁሉ በአንድ የሚያስተሳስረው ፍቅር ወዴት አለ?***
- ***በቤተችን ስላለ ፍቅር ስናነሳ የምንናገረው ስለ አራት የፍቅር ዓይነቶች ነው፡፡ እነርሱም፡- የትዳር ሕይወት ፍቅር፣ የወላጅ ፍቅር፣ የልጆች ፍቅር እና የወንድማማች ፍቅር ናቸው፡፡***

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

## *1. የትዳር ሕይወት ፍቅር*

- እግዚአብሔር ተጋቢዎችን በጽኑ ፍቅር ያስተሳስራቸው ዘንድ ካህኑ አክሊሉን በራሳቸው እያደረገ እንዲህ በማለት በጸሎተ ተክሊል ይጸልያል፡፡ ‹‹የጥበብና የማስተዋል አክሊል ትሁን አሜን፡፡ … እሊህ ባሮችህን ከክፉ ሐሳብና ምኞት ሁሉ ጠብቃቸው፣ ምሕረትህም በእነርሱ ላይ ትደረግ…፡፡››

*የባል ፍቅር ለሚስት*

- ቅዱስ ጳውሎስ ሚስቶቻቸውን ይወድዱ ዘንድ ‹‹ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ››*ኤፌ 5፡25፡፡* በማለት በምን ዓይነት ፍቅር እንደሚወዱም ጽፎላቸዋል፡፡
- ይህም ፍቅር ከመቀበሉ በፊት ዘወትር የሚሰጥ ፍቅር ነው፡፡
- ይህ ፍቅር የሚቀበለው ሰው ፍቅር ሊሰጠው የሚገባ ቢሆንም ባይሆንም የሚሰጥ ፍቅር ነው፡፡
- ባሉች በዚህ መንገድ በመውደድም እስከሞት ድረስ ታምኖ መሥዋዕት የሆነልንን፣ የወደደንን፣ እኛ በራቅነው ጊዜም እንኳ ‹‹አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው፡፡›› *ሉቃ 23፡34፡፡* በማለት የጸለየልንን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይመስሉታል፡፡
- ጌታችን በካድነውና ባልታመንለት ጊዜ ሁሉ በሰውነታን ድካም ያደረግነው እንደሆነ በመረዳት ወዶናል ይወደናል፡፡ እርሱ ፍቅር የባሕርይ ገንዘቡ ነውና፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ባሎችን ሚስቶቻችሁን ውደዱ ብሎ ሲመክር በውጭ ሲታዩ መልካም ቢመስሉም ፍቅርን አስመልክቶ በውስጣቸው ያለውን ተለዋዋጭነትና ከደካማነትም በቀላሉ የመሰበር ዕድላቸውን በመንፈስቅዱስ መነጽር ተመልክቶ ነው፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*የባል ፍቅር ለሚስት…*

- ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲሁ ‹‹እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው፡፡›› ***ቀዳ ጴጥ 3፡7፡፡*** በማለት መክሮአቸዋል፡፡
- ባል ሚስቱን ያለምንም ክፋት በደግነት ‹‹ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው፡፡›› ***ቆላ 3፡19፡፡*** የተባለውን ቃል በተግባር በመፈጸም መሆን ይኖርበታል፡፡
- በጸሎተ ተክሊል ‹‹አንተ የተወደድህ ወንድም ሆይ… የምታዝንላት ሁን፡፡ ልቡናዋን ደስ የሚያሰኛትን ነገር ሁሉ ለመሥራት ፍጠን፡፡ ከእናት ከአባቷ በኋላ ዛሬ በሷ ላይ አለቃ ነህና፡፡..›› በማለት ባሎች ታዘዋል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስም ይህንኑ ፍቅር ‹‹እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል፡፡ የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤›› ***ኤፌ 5፡28፡፡*** በማለት ገልጦታል፡፡
- በጋብቻ አንድ ሲሆኑ ባል አዳም ሔዋንን ‹‹ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል፡፡›› ***ዘፍጥ 2፡23፡፡*** እንዳለ በፍጹም ፍቅር ሚስቱን አጥንቴ፣ ሥጋዬ የሚልበት ፍቅር ይዋሃደዋል፡፡
- ባል ሚስቱን እንደራሱ አድርጎ ሳይሆን ወላጆቹን ጨምሮ ከሌላውም አብልጦ ሊወዳት ይገባል፡፡ ስለዚሁ ምክንያት ነው ‹‹ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡፡ ›› ***ዘፍጥ 2፡24፣ ማቴ 19፡5-6፣ ማር 10፡7-9፡፡*** ተብሎ የተጻፈልን፡፡

# <u>በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች</u>

*የባል ፍቅር ለሚስት…*

- ባል ሚስቱን መውደድ፣ ስለርስዋም መሥዋዕት የሚሆንና ትዕግሥት ያለው መሆን ይጠበቅበታል፡፡
- ‹‹ ልጆቼ ሆይ፥ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ፡፡›› ***<u>ቀዳ ዮሐ 3፡18፡፡</u>*** እንደተባለው ስሜቱን፣ ፍቅሩንና ፍላጎቱን ሳይደብቅ ሊገልጥላት ይገባዋል፡፡
- የሚስት ራስ ከመሆን ጋር አካል ያለ ራስ እንደማይሰራ ማስተዋል ይገባዋል፡፡
- አካል የሚያምረውና የሚንቀሳቀሰው በራስ አማካይነት ነው፡፡ ራስ እንደላከለት መልእክት አካል ምላሽ ይሰጣል፡፡
- ስለዚህ ሚስት ሥራ እየሠራች ከገቢው የምትጋራ ከሆነ ባል ይልቁኑ በቤት ውስጥ ሥራ ሊያግዛት ሊረዳት ይገባዋል፡፡

*ሚስት ለባልዋ ያላት ፍቅር*

- ሚስትም ለባልዋ ፍቅር ልትሰጥና ከአንድነት ፍቅር ልትሳተፍ ይገባታል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ራሳቸውን የሚሰጡበትን ፍቅር መጠን እንደሚከተለው ገልጦታል፡፡ ‹‹ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና፡፡ ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ፡፡›› *<u>ኤፌ 5፡22-24</u>*፣ ‹‹ሚስቶች ሆይ፥ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ፡፡›› *<u>ቆላ 3፡18</u>*፣ ‹‹ቆነጃጅትም የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ፥ ባሎቻቸውን የሚወዱ፥ ልጆቻቸውን የሚወዱ፥ ራሳቸውን የሚገዙ፥ ንጹሖች፥ በቤት የሚሠሩ፥ በጎዎች፥ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ ይምከሩአቸው፡፡›› *<u>ቲቶ 2፡4-5፡፡</u>*

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

## *ሚስት ለባልዋ ያላት ፍቅር*

- ሚስት በዕድሜ ከፍ ያለች፣ ከባልዋ የበለጠ የተማረች፣ ከባልዋ የበለጠ በተለያዩ ባሕላዊ ጉዳዮች ተሳትፎ ፈፊላት ብትሆንም ለመጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁም ባልዋን በሁሉ እንድትታዘዘው በጸሎተ ተክሊል ‹‹በሰፊ ልቡናና በንጹሕ ኅሊና ልትቀበይው ይገባሻል፡፡ በፊቱም ፊትሽን አታክፊበት፡፡ ከሚገባውም ነገር ሁሉ አንድ ነገር ስንኳን አታጥፊበት፡፡ ከሱ ጋራ በምትሠሪው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ፍሪው…›› ለታዘዘችው ትእዛዛት መታዘዝ ይጠበቅባታል፡፡
- ይህም በጸሎተ ተክሊል የተጻፈው ቃል ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹እንዲህ በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሔር ተስፋ ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ደግሞ ለባሎቻቸው ሲገዙ ተሸልመው ነበርና፤ እንዲሁም ሣራ ለአብርሃም፡፡ ጌታ ብላ እየጠራችው ታዘዘችለት፤ እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች እንኳ ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆችዋ ናችሁ፡፡» ***<u>ቀዳ ጴጥ 3፡5-6፡፡</u>*** በማለት እንደጻፈው በመንፈስ ቅዱስ በመቃኘት የተጻፈ ነው፡፡
- ባል ራሱን ለሚስቱ ቢሰጥ ምንም ስህተት የለበትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ይህንኑ አስመልክቶ ይህን ይለናል፡፡ ‹‹ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፡፡» ***<u>ገላ 3፡28፣</u>*** «ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም ያለ ሴት አይሆንም፡፡ ሴት ከወንድ እንደ ሆነች እንዲሁ ወንድ ደግሞ በሴት ነውና፤ ሁሉም ከእግዚአብሔር ነው፡፡» ***<u>ቀዳ ቆሮ 11፡11-12፡፡</u>***
- ቅዱስ ጳውሎስ ራስን የሚሰጡበትን ፍቅር አስመልክቶም ‹‹ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ፡፡ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ፡፡» ***<u>ቀዳ ቆሮ 7፡4-5፡፡</u>***በማለት ጽፎልናል፡፡
- በቀኖና ቤ/ክ መሠረት ሕዝባውያን ተጋቢዎች ሳይስማሙ አንዳቸው ተነስተው ወይም ቄስም ቄስም ቢሆን ለበለጠ አገልግሎት ሲል ያለሚስቱ ፈቃድ ወደ ገዳማዊ ሕይወት እንዲገባ አይፈቀድላቸውም፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*የመተጋገዝ ፍቅር*

- *ሚስት ባልዋን መውደደድ ብቻ ሳይሆን መርዳትም ይጠበቅባታል፡፡ ሔዋን የተፈጠረችበትም ዋናው ዓላማ አዳምን እንድትረዳው ነውና፡፡ ዘፍጥ 2፡18፡፡*
- *እግዚአብሔር ለሚስት የሰጠው ልዩ ስጦታ ቢኖር እንድትመካበት ሳይሆን በሥራው ሁሉ እንድትረዳው መሆኑን ማወቅ ይገባል፡፡*
- *እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ለሴት ብቻ የሰጠውንና በስጦታውም ባልዋን እንዴት እንደረዳች የሚያመለክተውን መልዕክት እናገኛለን፡፡*
- *ይህም አቢግያ ሰነፍ በነበረው ባልዋ ቦታ ሆና በንጉሥ ዳዊት ፊት ባደረገችው ቁምነገር ተገልጧል፡፡ ‹‹ በእግሩም ላይ ወደቀች፥ እንዲህም አለች፡፡ ጌታዬ ሆይ፥ ይህ ኃጢአት በእኔ ላይ ይሁን እኔ ባሪያህ በጆሮህ ልናገር፥ የባሪያህንም ቃል አድምጥ፡፡… የእግዚአብሔርን ጦርነት ስለምትዋጋ እግዚአብሔር በእውነት ለጌታዬ የታመነ ቤት ይሠራልና የእኔን የባሪያህን ኃጢአት፥ እባክህ፥ ይቅር በል በዘመንህም ሁሉ ክፋት አይገኝብህም፡፡›› ቀዳ ሳሙ 25፡24፣28፡፡*
- *ባልዋ በትምክህት ስላደረገው ነገር ፈንታ በትሕትና በንጉሥ ዳዊት ፊት ተደፍታ ‹‹ጌታየ›፣ ‹‹ባሪያህ›› የሚሉ ቃላቶች በመጠቀም ቀረበች፡፡*
- *ሁሉም ሚስቶች ለባሎቻው እንዲከብዱባቸው ሳይሆን እንዲረዱአቸው እንጠይቃለን፡፡*
- *ሚስቶች ሆይ ልጆችንና ገቢያችሁን በማሳደግ ባሎቻችሁን እርዱ፡፡*
- *ሚስቶች ሆይ የምትወስኑትን ውሳኔ በጋራ፣ በትሕትና፣ በማስተዋል የነፍሳችሁን ድህነት በማታጠፉበት መልኩ ወስኑ፡፡ ባሎቻችሁም በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲድጉ እንቅፋት አትሁኑባቸው፡፡*

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

### *የመተጋገዝ ፍቅር*

- በመጽሐፍ ቅዱስ ስለመልካም ሴት ‹‹*ዕድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርግለታለች፥ ክፉም አታደርግም።* … በእጆችዋም ደስ ብሎአት ትሠራለች። … የቤትዋንም ሰዎች አካሄድ በደኅና ትመለከታለች፥ የሀኬትንም እንጀራ አትበላም። ልጆችዋ ይነሣሉ፥ ምስጋናዋንም ይናገራሉ ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል።መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፥ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ። ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች። ከእጅዋ ፍሬ ስጡአት፥ *ሥራዎችዋም* በሸንጎ ያመስግኑአት።» ***ምሳ 31፡12-31፡፡*** ተጽፎልናል፡፡
- ተጋቢዎች በፍጹም ፍቅር ተሳስረው፣ ፍቅራቸውም ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቀር ነጸብራቅ ሆኖ ለእግዚአብሔር ያላችሁን ፍቅር የሚገድብ እንዳይሆን ይጠንቀቁ፡፡
- በባልና በሚስት መካከል ያለ ፍቅር ሊጎዳ የሚችልባቸው በርካታ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ከሚጠቀሱትም መካከል ጤናማ ያልሆነ ፍቅር ይገኛል…
  - ሔዋን ለአዳም የነበራት ፍቅር፡- ሔዋን ለአዳም ከነበራት ፍቅር የተነሳ ከተከለከሉት ዛፍ ፍሬ ወስዳ ብዙ ዋጋ ያስከፈለውን ያለመታመንን ፍሬ አቀመሰችው፡፡ ይህም ፍቅር አዳም ለእግዚአብሔር የነበረውን ፍቅር የገደበ ያደናቀፈ ፍቅር ነበር፡፡ ***ዘፍጥ 3፡፡***
  - የኤልዛቤል ፍቅር፡- ለባልዋ ለአክአብ የነበራት ፍቅር ከእግዚአብሔር ፍቅር የወጣ ነበር፡፡ በዚህም የእውርነት ፍቅር አክአብን ገዝታው የድሃውን የናቡቴን መሬት እንዲነጥቅ ከማድረግዋም በላይ ተጨማሪ ክፋትን እንዲፈጽም አብቅታዋለች፡፡ እግዚአብሔርም «*ሚስቱም ኤልዛቤል እንደ ነዳችው፥ እንደ አክዓብ ያለ ሰው አልነበረም።*» ቀዳ ነገ 20፡25፣ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ገድለህ ወረስኸውን? ብለህ ንገረው። ደግሞም፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል» በማለት የተናገረበት አክአብ ነበር፡፡ ***ቀዳ ነገ 20፡19፡-25፡***

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*የመተጋገዝ ፍቅር…*

- ሐናንያና ሰጲራ፡- ይፋቀሩ ነበር፤ መሬታቸውንም ሸጠው ለሐዋርያት ለመስጠት ተስማሙ፡፡ ፍጹም በሆነ ፍቅር መጉደል የተነሳ ግን መንፈስቅዱስን በሐዋርያት ፊት ለመዋሸት/ለማታለል ተስማሙ፡፡ በዚህም የተነሳ በውጤቱ ሁለቱም ተጎዱ ሆኑ፡፡ ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ገድለህ ወረስኸውን? ብለህ ንገረው፡፡ ደግሞም፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ገድለህ ወረስኸውን? ብለህ ንገረው፡፡ ደግሞም፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል፡፡›› *የሐዋ 5፡9-10፡፡* ይህንም አስመልክቶ ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ገድለህ ወረስኸውን? ብለህ ንገረው፡፡ ደግሞም፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል፡፡›› *ምሳሌ 14፡1፡፡* በማለት ጽፎልናል፡፡
- ስለዚህ ሚስቶች ፍቅር አስመስለው ለክፉ ነገር ሳያነሳሱ፣ ይልቁኑ ለእግዚአብሔር ስላላቸው ፍቅር ክፋትን እንዳያደርጉ በመጠበቅና ለበጎ ነገር በማገዝ ባሎቻቸውን በጌታ በእግዚአብሔር እንዲወዱ እንመክራለን፡፡
- ጻድቁ ኢዮብ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ሲፈተን ‹‹ሚስቱም፡፡ እስከ አሁን ፍጹምነትህን ይዘሃልን? እግዚአብሔርን ስደብና ሙት አለችው፡፡›› *ኢዮ 2፡9፡፡* ኢዮብ ያደረገው ግን ‹‹እርሱ ግን አንቺ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፥ ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን? አላት፡፡ በዚህ ሁሉ ኢዮብ በከንፈሩ አልበደለም፡፡›› *ኢዮ 2፡10* ተብሎ ተነግሮናል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*የመተጋገዝ ፍቅር...*

- ባሎች ሚስቶቻቸው ቃላቸውን የማይሰሙ እግዚአብሔርንም የማይፈሩ ቢሆኑ በተቻላቸው ሁሉ መጠን ሚስቶቻቸውን ወደ በጎ መምራት እንጂ ክፉ ምክራቸውን መቀበል አይገባቸውም። ሣራ ለአብርሃም ከነበራት ፍቅርና መታዘዝ የተነሳ አቤሚሌክን ለአብርሃም እህቱ ነኝ በማለት ለአብርሃም የነበራት ፍቅርና ታማኝነት ከእግዚአብሔር እንደበለጠባት ሆኖ መገኘት አይገባም።
- ባለትዳሮች ፍቅራቸው በዓለም ከሚታየው የላቀና የበለጠ ሆኖ መገኘት ይገባዋል። ይህም መካን ሆና ሳለች ሚስቱን ይወድ የነበረና ይህንኑም በተግባር እንዳሳየ እንደ ካህኑ ዘካርያስና የሆነውን ሁሉ በጸጋ በመቀበል በታማኝነት እንደኖረች እንደ ቅድስት ኤልሳቤጥ ሊሆን ይገባል። ‹‹ሁለቱም በእግዚአብሔር ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ።›› ሉቃ 1፡6። ተብሎ እንደተገለጠ።
- በርካታ መንፈሳውያን አገልጋዮችም አጀማመራቸው የቀና ቢሆንም የትዳር ጓደኞቻቸውን እንዴት ደስ እንደሚያሰኙ በሥጋ በማሰብ ብቻ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግኑኙነትና የነፍሳቸውንም ነገር ይዘነጉታል።
- ታዲያ በፍቅር፡ እንዲሁም በትዳር ፍቅር የተሸለመችው ቤተ ክርስቲያን በቤታችን ትገኝ ይሆን?

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org